# *<u>ማንን እንመን?</u>*

ይህ ጥያቄ እኔ ባደባባይ ላውጣው እንጅ በያሉበት ሆነው ባንድ ጉዳይ ላይ የተለያዩ ነገሮችን የሚዘበራ
ርቁትን ጳጳሳት መምህራንየሚሉትን በቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ ያለውን ብቻ ሳይሆን በሩቅና በቅርብ
ያለውን ተመልካች እየታዘባቸው አማኙን እያሳዘነ ነው። በየቤተ ክርስቲያን በህዝብ ፊት እየቆሙ የሚ
ያሰራጩት መዘበራረቅ የማያመውና የማይሰማው እኔ ምና ገባኝ ብሎ ዝም የሚል ክርስቲያንእንደምን ያ
ለ ክርስትና ነው? የሚል ጥያቄ ከተለያየው ህዝብም በየቦታው እያስነሳ ነው።

የውጩ የኢትዮጵያ ሲኖዶስ የቀድሞው ቆሞስ አባ ወልደ ትንሳዔ ያሁን ሊቀ ጳጳስ አቡነ በርናባስ
“ክርስቶስ በሥጋው ፍጡር ጠበቃ አማላጅ ነው” ይላሉ።
የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን እወክላለሁ የሚሉት ሊቀ ጳጳስ አቡነ ፋኑኤል ፤ <u>“የውጩ ሲኖዶዶስ
ክርስቶ በሥጋው ፍጡር ነው ስለሚል ከእንግዲህ እርቅ የለም”</u> ይላሉ።
የውጩ የኢትዮጵያ ሲኖዶስ ስያትል የሚኖሩ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ሉቃስ የሚባሉት በበኩላቸው የራሳቸው
ሲኖዶስ አባል የሆኑትን “አቡነ በርናባስን እስልምና እንኳ ፈራጅ ብሎ አያምንም ክደው አማላጅ ነው
በማለታቸው መናፍቅ ናቸው” ብለው አውገዘዋል።

ቆሞስ አባ መአዛ በየነ የሚባሉትም ቤተ ክርስቲያናችን ከምትለው ውጭ የሚወቀሱባቸውና የሮማ
ካቶሊክን እስታቹ በቤተ መቅደስ መተከልንና ብዙ የዘበራረቁት እንዳለ ሆኖ፤ አሁን በተነሳው ነገርም፤
እነ ዶክተር አክሊሉን እየጠቀሱ ተከሰተባቸው እያሉ አቡነ በርናባስን በመደገፍ ይናገራሉ።
በገለልተኝነትን ሽፋን በማድረግ ለሳቸው የተመቻቸውንና ደስ ያላቸውን ብቻ እየመረጡ ነው ማለት
ነው የሚናገሩት? አሁን የሚናገሩትን ትክክል ይሁኑ አይሁን ሊመሰክሩላቸው የሚችሉት ባንዲት
ቅንጣት ብቻ የሚስማሟቸው ሰዎች ካልሆኑ ማነው የሚመሰክርላቸው። በግላቸው ስለሚያደርጉት
ያፈነገጠ ነገር ትክክል ስለመሆናቸው ማነው የሚያረጋግጥላቸው? ከማን መምህር ከየት ጉባዔ
ተማሩት?

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ የሚባሉትም፡- የኛ ሊቃውንት አባቶች የማይጠቅሷቸውን የጣሊያኖችን ሰዎችና
እነሱ የሚሉትን እየደረደሩ አኀት አብያተ ክርስቲያናትናት ከነሱና ከእሱ እንዲማሩ በድፍረት እየተናገሩ
ነው። ይህም ባብነቱ ትምህርት ነበርን በሚሉ ሁሉ ትልቅ ውርደት ያስከተለባቸው ወቅት ነው።
የተዘበራረቀ የሚናገሩት ሁሉ የሊቃውንት ጉባዔ የሚባለው ጭራሽ እነደሌለ ነው።
የተመለከተውን ሁሉ እያስገረመው ነው። ተሃድሶዎች ጋር በውጊያ ስንጠመድ ሳናውቀው ቀኝ እግራችን
ካቶሊኮች ግቢ ዘው ብሎመግባቱን ይሆን?

መጋቤ ሐዲስ ሮዳስ ስለ እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ንጽህና የAugustine "Immaculate
Conception" በኋላም 1854የሮማ ካቶሊክ Pope
Puis ዶክትረን አድርጎ የወሰነውን የኦርቶዶክሶች እምነት ነው አትናትዮስም ከሺህ አመት በፊት የተናገረ
ው ነውእያሉን ነው ካቶሊካዊ አገላጽ እና ፍጽም ከኦርቶዶክስ ያልሆነና አትናትዮስም “On the
Incarnation by St.
Athanasius” በሚለውመጽሃፉ ውስጥ የማይገኝ ነው። ይህንን የAugustine የስህተት ትምህርት መ
ላው ኦርቶዶክሳውያን በተለይም ከእኛ ጋር የእምነት አንድነትያላቸው Oriental Churches
(አሃት አብያተ ክርስቲያናትን) በፍጹም እንደማይቀበሉት የካቶሊክ ብቻ እምነት እንደሆነ ሳይገልጹጭራ
ሽ የአትናትዮስም እምነት ነበር አሉን ካቶሊቶሊኳዊውን እምነት የእኛ
የኢትዮጵያ ኦርቶዶክ ቤተክርስቲያን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክቤተክርስቲያን ለማድረግ ነውን !

በዚህች አጭር ጽሁፍ የተገለጹት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚታየውን ወዲህ ወዲያ
ወዲህ የተዘበራረቀ ነገር እየተናገሩ እርስ በርሳቸው በመደባደብ ህዝቡን የርስ በርሳቸው መደባደቢያ

ብትር የሚታገሉበት ሜዳ አደረጉት። ከማዳመጥ በቀር የምትናገሩትን ሁሉ ከየት አመጣችሁት? ብሎ ህዝቡ እንደማይጠይቃቸው ተረድተው፡ በዚችየኢትዮጵያቤተ ክርስቲያን ፤ በመነኩሴ በጳጳስ በሰባኪ ስም ራሱን ሸፍኖ በመደባደብ እየዞሩ ህዝቡን በመከፋፈል ችግሩን እያጋጋሉ እያሰለቹን ቤተ ክርስቲያንን እያናወጣት ያለው የተዘበራረቀ ንግግራቸው ግራ ለተጋባነው ማነው እውነቱን ሊገልጽልን የሚችለው? የጥንት ሊቃውንት ያብነቱ መምህራን ይህን የተዘበራረቀ ነገር እንዴት ያስተካክሉትና ያስታርቁት ነበር?ማነው የዋሸው?

የሚነገረንና የምንሰማው ምንድነው? ወዴትስ እየተመራን ነው? እርስ በርሳቸው በሚደርጉት ሽኩቻ ከ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ነገረ መለኮት ራሳቸው እየሳቱና ህዝቡንም እያሳቱናቸው። ለቅድስና መወዳደርና መነጻጸር እጅግ አስፈላጊ ቢሆንም፤

ቅዱስ ጳውሎስ እራሳቸውን ከገዛ ራሳቸው ጋራ እያነጻጸሩ እኛ ብቻ በማለት እራሳቸውን እያገነኑ ከተግዳሮት እንደወደቁ ሰዎች አንሁን። ራሳቸውን ከራሳቸው ጋራ የሚያነጻጽሩ ሰዎች የሚናገሩትን አያውቁም" ብሎ ያስጠነቀቀውን ባለመርሳት፤

"በገዛ ደሙ የዋጃትን የእግዚአብሄርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመባት ለመንጋው ተጠንቀቁ ። ከሄድኩህ በኋላ ለመንጋው የማይራሩ ጨካኞች ተኩላዎች እንዲገቡባችሁ ደቀ መዛሙርትን ወደ ኋላ ይስቡ ዘንድ ጠማማ ነገረን የሚናገሩ ሰዎች በመካከላችሁ እንዲነሱ እኔ አውቃለሁ" ( የሐዋ ፳፡፳፰—፴) እያልን ወደፊት የሚከሰተውን ሳይቀር እየተናገርን እንደ እነ ቅዱስ ጳውሎስ፤ ያለፈውን ካለው ጋራ እያነጻጸርን፤ ዘመናችንን እየዋጀን፤ የሚመጣውንም እየገመትን፤ የተኩላ ባህርይ ካላቸው ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን በትጋትና በቅድስና ለመጠበቅ በታሪክ የሰማናቸውን እንደነ አቡነ ጴጥሮስ የነበሩትን ሰማእታት

ሳንረሳ፤ ክርስቶስ የዮሐንስን ደቀመዛሙርት አነጋግሮ ከሸኘ በኋላ ሰዎች ከእምነቱና ከወቅታዊው ች ግር ጋራ የማይገናኝ ነገር ሲነጋገሩ ሰማና "ነፋስ የሚወዘውዘውን ሸምበቆ ወይስ ቀጭን ዋብስ የ ለበሰው ሰውለማየት ነው የመጣችሁ?" እያለ አቋም የለሽነታቸውንና አላማ ቢስነታቸውን በምሬት ነገራቸዋልና።

ቀሲስ

አስተርአየለመሆኑ እርሰዎ እንዴትስ ያስታርቁታል? በእምነታችን ላይ የዘራውን የጥርጣሬ መንፈስእን ዴት ይመለከቱታል? መታለፍ በሌለባቸው ነገሮች ላይ፤የግብጽ ይህን ይላል አኀት አብያተ ክርስቲያናት ይህን ይላሉ፤ የሮማ ካቶሊኮች ይህን ይላሉ፤ ከማለተዎ በፊት ከዚህ ቀደም እንደሚያደርጉት አስተማሩኝ ከሚሏቸው ሊቃውንት አባቶች የተማሩት ካለ ይንገሩን። የተነሳውን ዝብርቅርቅ አብራርተውና አፍታተው ለመግለጽ ካቅመዎ በላይ ከሆነ፤ የማያውቁትና ያልተማሩት ከሆኑ አንዳንድ ጊዜ ዝምታ ወቅ ነውና በዝምታወ ይቀጥሉ።

ዝምታ ወርቅ ነው የሚባለው ባላወቁትና ባልተረዱበት ነገር እንደ ሰንበት ተማሪዎች ዘሎ መግባትን ለመቃወም እንጅ፤ የተማሩትንና ያመኑትን፤ ውሎ አድሮ ለህዝብ መገለጡ አይቀርምና ቢገለጥ የማያሳፍረውን የመናገር ደግሞ የሊቃውንት የምሁራን የክርስቲያኖች ነውና።ምን ብሎ እንዲጠይቅ የሚያደርግ ነው። ይልቁንም የቤተክርስቲያኒቱ አካል ነኝ ለሚል በግሌ ምን ማድረግ ይገባኛል? ብሎ ራሱን እንዲጠይቅ የሚገፋፋና የሚያስገድድ ይመስለኛል።

የተዋህዶው ሃይማኖት እምነት መሠረትየሆነው ነገረ መለኮት የተዛባበት

ጥያቄ ላይ የወደቀበት ወቅት ነውና።

ይህ የምንገኝበት ዘመን እጅግ አስፈሪና አስደንጋጭ ጥያቄ ይቀሰቅሳል። እምነቱና ችሎታው ሳይኖራቸው ከቦታው ጋራ የተገናኘውን ክብርናጥቅም ለመሰብሰብ ሲሉ እየዘለሉ በገቡ ሰዎች ላይ የሚመጣው ፍርድ እጅግ በጣም ያስፈራል።ይህ የሜዳ ጨዋታ አይነት
ጫጫታናሁካታባቢሎናዊ ዝብርቅርቅ ምስቅልቅል *ማንን እንመን?*

*ሰላም! ሻሎም!*
*ገብርኤል ብዙነጎ*